Bag it RIGHT
Prince George's County

Angela D. Alsobrooks
County Executive

Prince George's County Department of the Environment

Prince Georges County, MD Proud Get to Know Us

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

## የ Better Bag Bill ዓላማው ምንድን ነው፧

አንዴ ጥቅም ላይ ውለው በሚጣሉ የዕቃ መያዢያ ቦርሳዎች አማካኝነት የሚፈጠር ቆሻሻን በመቀነስ እንዲሁም እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ የዕቃ መያዢያ ቦርሳዎች ስለሚሰጡት ጥቅም ለሸማቾች ግንዛቤ በመፍጠር የሰው ጤናን፣ የእንስሳት እና የባህር ውስጥ ህይወትን ጨምሮ አካባቢን ለመጠበቅ። የፕላስቲክ ከረጢቶችን ስርጭት በመገደብ እና የችርቻሮ መደብሮች ለወረቀት ወይም ድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ ለሚችሉ ቦርሳዎች ቢያንስ 10 ሳንቲም ሸማቾችን እንዲያስከፍሉ በማድረግ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን እና በፍሳሽ መተላለፊያ መስመሮች ላይ የሚፈጠር ብክለትን እንቀንሳለን።

## ይህ ህግ በየትኞቹ ንግዶች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፧

ሁሉም የችርቻሮ መደብሮች፣ ሬስቶራንቶች፣ የግሮሰሪ መደብሮች፣ ወይም ለሚሸጠው ምርት ወይም ለሚያቀርበው አገልግሎት አንዴ ብቻ ጥቅም ላይ ውለው የሚጣሉ የፕላስቲክ ቀረጢቶችን የሚሰጥ ለትርፍ የተቋቋመም ይሁን ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም።

## ህጉ መቼ ተግባራዊ ይሆናል፧

ከጃንዋሪ 1፣ 2024 ጀምሮ፣ ቸርቻሪዎች ለደንበኞቻቸው የፕላስቲክ ከረጢቶችን ማቅረብ አይችሉም።

የህጉ ድንጋጌዎች በተግባር ላይ ከዋሉ በኋላ ላሉት ለመጀመሪያዎቹ **90 ቀናት** ተቆጣጣሪው የገንዘብ ቅጣት የያዘ ኦፊሴላዊ ሰነድ (citation) አይሰጥም። ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የሚያዝ ማሳሰቢያ (correction notice) ሊሰጥ ይችላል እንዲሁም ማንኛውንም በ CB-32-2023 ህግ ድንጋጌዎች ውስጥ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የማያሟሉ የችርቻሮ መደብሮችን ለማስተማር ይሞክራል።

## ከወረቀት ለተሰሩ እና እንደገና ጥቅም ላይ ለሚውሉ ቦርሳዎች ለምን በትንሹ የ 10-ሳንቲም ክፍያ ተጣለባቸው፧

በችርቻሮ መደብር በሚቀርቡ የወረቀት እና እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ በሚችሉ ቦርሳዎች ላይ ክፍያ መጣሉ ደንበኞች የራሳቸውን የዕቃ መያዢያ እንዲያመጡ ያበረታታል እንዲሁም አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ የዕቃ መያዢያ ቀረጢቶችን ፍላጎት ይቀንሳል። የወረቀት ከረጢቶችን እና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቦርሳዎችን ለመግዛት እና አማራጮችን ለማቅረብ ያወጣው ወጪን ለማካካስ ቸርቻሪው ክፍያውን ሙሉ በሙሉ ይወስዳል/ለራሱ ያስቀራል።

ደንበኛው ለመግዛት ለወሰነው ለእያንዳንዱ ከረጢት ቸርቻሪው የሚያስከፍለው ክፍያ በደንበኛው ደረሰኝ ላይ፣ ልክ እንደሌሎች ሸቀጦች ለተይቶ የሚቀመጥ ይሆናል። ተቋማት/መደብሮች በደንበኞች መግቢያ በር ወይም በእያንዳንዱ የሽያጭ ቦታ ላይ የቀረጢት ክፍያን የሚመለከት ማስታወቂያ መለጠፍ አለባቸው።

## እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ቦርሳ የሚባለው የትኛው ነው፧

እንደገናጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የዕቃ መያዣ ከረጢት በተለየ መልኩ የተነደፈ እና በተደጋጋሚ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውል እንዲሁም (1) ከፕላስቲክ ሳይሆን ከልብስ ወይም ሌላ ሊታጠብ ከሚችል ጨርቅ፣ ወይም (2) በተደጋጋሚ መልሶ ጥቅም ላይ ሊውል ከሚችል ከጠንካራ/ከዘላቂ ቁሳቁስ የተሰራ እና የተሰፋ እጀታ ያለው ቦርሳ ተብሎ ይገለጻል።

## ደንቡ ተግባራዊ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ፧

ለሚከተሉት አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ለሚውሉ የዕቃ መያዢያ የወረቀት ቦርሳዎች ተቋማት ደንበኞችን ክፍያ አያስከፍሉም/አይጠይቁም፦

- ከፋርማሲ ለሚገዙ መድኃኒቶች የሚሰጡ መያዣዎች።
- የተዘጋጁ ምግቦችን በመኪና መስኮት (drive-through window) በማቅረብ ለሚሰጥ መስተንግዶ የሚውል ማሸጊያ።
- ከምግብ በኋላ ደንበኞች የተረፋቸውን ምግብ ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ በት በተሟላ አገልግሎት አቅራቢ ሬስቶራንት የሚሰጥ የማሸጊያ ዕቃ።

በተጨማሪም፣ በፕላስቲክ ከረጢቶች ላይ የተጣለው ክልከላ ለሚከተሉት አገልግሎቶች ጥቅም ላይ በሚውሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች ላይ ተግባራዊ አይሆንም፦

- ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ለውዝ፣ እህል፣ ከረሜላ ወይም ትናንሽ የሃርድዌር ዕቃዎችን ጨምሮ ሌሎች የጅምላ እቃዎችን ለማሸግ።
- የታሸጉም ሆነ ያልታሸጉ የቀዘቀዙ ምግቦችን፣ ስጋን ወይም አሳን ለመጠቅለል።
- አበቦችን፣ በማሰሮ ውስጥ ያሉ አበቦች፣ ወይም ሌሎች እቃዎች ለመጠቅለል።
- ያልታሸጉ የተዘጋጁ ምግቦችን ወይም የዳቦና ኬክ ምርቶችን ለመያዝ።
- ጨርቃጨርቅ ወይም የደረቁ-ንጹሕ አልባሳትን ለመከላከል ወይም ለመያዝ፤ ሙሉ ልብሶችን፣ ቀሚሶችን፣ እና መደበኛ አልባሳትን ከቆሻሻ ለመከላከል።
- ከችርቻሮ መደብር በህይወት ያለ ዓሳን፣ ሶስት አፅቄዎችን፣ ሞለስከሶችን ወይም ክረስቴሻንስን ለመውሰጃ።

## ካውንቲው እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቦርሳዎችን ለነዋሪዎች ያቀርባል፧

ካውንቲውበልዩ ዝግጅቶች ወቅት በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ውስን ነፃ የዕቃ መያዢያ ቦርሳዎችን ለነዋሪዎች፣ ቀድሞ የመጣ፣ ቀድሞ ይወስዳል በሚለው መስፈርት መሰረት ያሰራጫል። በተጨማሪም፣ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቦርሳዎችን በተቋሞቻቸው ውስጥ ማሰራጨትን ሊመርጡ ይችላሉ።

## ይህ ግብር ነው፧

አይደለም። ለወረቀት ወይም ዳግም ጥቅም ላይ ለሚውሉ ቦርሳዎች የሚከፈለው ዝቅተኛው የአስር ሳንቲም ክፍያን የሚያስከፍለው እና በቀጥታ ክፍያውን የሚሰበስበው ቸርቻሪው ሲሆን ክፍያው የሚከፈለው ድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና የወረቀት ቦርሳዎችን ለመግዛት እና የወጡ ተያያዥ ወጪዎችን ለማካካስ ነው። መንግስት ከቦርሳ/ከዕቃ መያዣ ሽያጭ ከተሰበሰበ ክፍያ ላይ ምንም አይነት ገንዘብ አይቀበልም።

## ለምገዛቸው ቁሳቁሶች ቦርሳ መጠቀም አለብኝ፧

ክፍያን ለማስቀረት ሸማቾች ለሸመታ ወደ መደብር በሚሄዱበት ጊዜ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቦርሳዎችን ይዘው ወደ መደብር እንዲያመጡ ይበረታታሉ። አንዳንድ መደብሮች ሸማቾች ዕቃዎቻቸውን ለመጠቅለል የሚጠቀሙባቸውን የካርቶን ሳጥኖችን ሊያቀርቡ ወይም አንድ ሰው የራሱን ሳጥን ሊያመጣ ይችላል። ካርቶን ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል እና እንደገና ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ጠፍጣፋ መሆን አለበት።